# የኤርትራ ጉዳይ ግራ ገብቶን ግራ እንዳናጋባ እሠጋለሁ

**ቢፍቱ ቢያ**

ሰሞኑን በኢትዮጵያ ዛሬ ፣ በአንዳንድ ድረ ገፆችና ፓልቶክ ክፍሎች ውስጥ ለኢትዮጵያዊነታቸውና ለኢትዮጵያ ቅን አሳቢ ለመሆናቸው ምንም ጥርጥር የሌለኝ ፤ አርቆ አሳቢና የዋህ ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያ ካላቸው በጎ ምኞት የተነሳ የራሳቸው የሆነውንና ሌላውም ይጋራናል ያሉትን አስተያየቶች ሲሰያስደምጡንና ሲያስነብቡን ከርመዋል ። በግልጽ "ኤርትራዊ ነን" ያሉትንም ዜጎች የመናገር ዕድል ሰጥተው ያላቸውን ሃሳብ እንዲያካፍሉን አድርገዋል ። በእውነቱ የሁሉንም ወገን ሃሳብ የማንሸራሸሩን ልምድ አረንጓዴ መብራት ሰጥቼው ሳልፈው "በኤርትራ በኩል መደራጀት ይቻላል ወይ? ለኢትዮጵያ አንድነት ፣ ዴሞክራሲ ፣ ነጻነት ፣ እኩልነትና ፍትህ" የሚያስብ ወይም በፖለቲካ ፕሮግራሙ ላይ ይህንን በጉልህ አስምሮ የሚንቀሳቀስ የፖለቲካ ድርጅት "በእውነት በኤርትራ በኩል ከነድርጅታዊ ነጻነቱ መንቀሳቀስ ይችላል ወይ? . . . ." የሚለው ጥያቄ ኢትዮጵያዊ አንጎላቸውን ካዞራቸው ወገኖች አንዱ ሆኜ የራሴን ለማለት እነሆ ጀመርኩኝ ።

በኤርትራ በኩል ወደ አዲስ አበባ የሚያቀና የትግል ኮሪደር ወይ ፔዲዮ ማግኘቱ የከፋ አይደለም ። ግን ፣ የኤርትራ አስተዳደር ያ ሁላችንም የምናውቀውን ባህሪውን ለውጧል ወይ? ነው ዋናው ጥያቄ ። እንደሚታወቀው የኤርትራ አስተዳደር ለኢትዮጵያ በዘር ላይ የተመሰረተ የአስተዳደር ግዛቶች መፈብረክና በጎሳ ላይ የተንተራሱ ራእይ አልባ የፖለቲካ ድርጅቶች መቀፍቀፍ ዋና ምክንያት ከመሆኑ ባሻገር በጊዜው የነበሩት የአንድነት ኃይሎች በኢትዮጵያ የፖለቲካ ኳስ ሜዳ ውስጥ ገብተው የበኩላቸውን እንዳይጫወቱ ከፍተኛ አረንቋ የፈጠረ አስተዳደር ነው ። ከወያኔ በላይ ሆኖ ፣ የወያኔ መንግሥት መዘውር ሆኖ ፣ ጀሌው በነበረው ወያኔ አማካኝነት በኢትዮጵያ ታሪክ ኢትዮጵያን ለማፈራረስ እንቅልፍ አጥተው እልህ አስጨራሽ ፀረ-ኢትዮጵያ ተግባር ከፈጸሙ ኃይሎች ሁሉ የከፋውንና የበለጠውን ወደር አልባ ሚና የተጫወተ አስተዳደር ነው - ሻዕብያ ። ያ ባህሪው ጫካ በነበረበት ወቅት የነበረ ፤ ከነጻነት በኋላና ከባድሜ ጦርነት በፊት የቀጠለ ፤ ከባድሜ ትርጉም አልባ ጦርነት በኋላም ያልተወው ነው ። አሁንም በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የሚያሳየው ያንኑ ሁላችንም የምናውቀውን የአደባባይ ምስጢር ነው ።

በኤርትራ በኩል የትጥቅ ትግል መጀመር ውጤት የለውም ብዬ አራት ነጥብ ላይ አልደረስኩም ። ከሻዕብያ የትዕቢት ፣ የእብሪት ፣ የንቀት ፣ የማናለብኝነት ፣ የጉራ ፣ የገዳይነትና አብሮት ካደገው የሃሰት ባህሪ አንጻር ስንገመግመው ፤ በአስመራ ደጋፊነት ፣ መሬት ሰጪነት ፣ ትጥቅና ስንቅ አቀባይነት የመተኮስ ትግልን በኤርትራ በኩል ማጧጧፉን የመጨረሻ ምርጫ አድርጎ መደምደሙና በዚያው ድምዳሜ ለለውጥ ወደ ዘመቻ ማቅናቱ የሆነ ብዥታ ማጫሩ አይቀርም ። ምክንያቱም ያንን ብዥታ ሊያጠራ የሚችል ይፋዊ መግለጫ የኢትዮጵያ ህዝብ ከኢትዮጵያ ሰሜን አቅጣጫ ከምትገኘዋ ከኤርትራ አስተዳደር በኩል አልሰማም ። ማለዳ ጎህ ሲቀድ ጀምሮ ጀምበር እስክታሽቆለቁል ድረስ ፣ ከጀምበር መጥለቅ እስከ ፀኃይ መውጣት ድረስ ከአርባ አምሥት ዓመታት በላይ ፀረ-ኢትዮጵያ አጀንዳን ሲነሰንስ የነበረ ድርጅት ዛሬ ያሰበው ሁሉ አልሳካ ሲለው በተለያዩ የመገናኛ መሳሪያዎቹ የሚያሰራጨውና እኛም የምንሰማውና የምናየው ፖለቲካዊ ቧልት ሲዲ የሚመስለው ፤ አንዳንዴ ደግሞ ሜድ ኢን ያፍሪካ ቀንድ የውሸት ምስል የሚመስለው ፊልም መሰል መግለጫና ዜና የሻዕብያን አቋም ቁልጭ አድርጎ አመላካቷል ማለት የሚቻልበት የመጨረሻ ሳይሆን የመጀመሪያ ደረጃ ሚዛን ላይ እንኳ አላደረሰም ።

መሳሪያ ታጥቆ የመግደልና የመገደል ትግልን በኤርትራ በኩል ለማድረግ ሻዕቢያ ገርበብ ያደረገላቸውን በር ተጠቅመው ኢትዮጵያዊ አጀንዳዎችን ለማራመድ በኤርትራ መሬት ላይ የተሰማሩ ኢትዮጵያውያን ኃይሎች በእውነት ከነኢትዮጵያዊ አጀንዳቸው ትግላቸውን ቀጥለዋል? …. . ወይስ እንደቀጠሉ ነው? …ከምናውቃቸው ኢትዮጵያዊ ታጋይ መሪዎች ወይም ባለተስፋዎች መሃል ስንቶቹ ታስረዋል? ስንቶቹ ተገድለዋል? …በእውነቱ ይህን ለማወቅ አስቸጋሪ ነው ። በራሱ የተደላደለ የምጣኔ ሃብት የሌለው ፤ ከአንድ የእለት ጉርሱን ብቻ ከሚያሳድድ ደሃ ዜጋ ጋር የሚመሳሰ ል የኤክስፖርት ሃብት አቅም ካለው የሻዕብያ

መንግሥት ጉያ ሥር ተጠልሎ ለኢትዮጵያ ህዝብ በእውነት ለእውነት መታገል የማይታመን ነው የሚመስለው ። ምክንያቱም የሻዕብያ ባህሪ እንደዚያ ነው ። ከልጁ ከወያኔ ይበልጥ እንደሆን እንጂ በምንም መለኪያ ከወያኔያዊ ባህሪ አያንስም - አባት ሻዕብያ ። ሻዕብያ' ኮ እንኳን ዛሬ "የኤርትራ መንግሥት መንቀሳቀሻ መሬት ሰጥቶናል" ብለው ዘለው ወደ አሥመራ የመሄጃ ብቻ የአውሮፕላን ቲኬት ቆርጠው (ካለመለስ) የገቡትን ኢትዮጵያዊያንን ሳይሆን የትግል አጋሮቹን ፣ አብረው የክላሽ ምላጭ ሲስቡ የነበሩትን ፣ ባሩድ ሲያሸቱና በዲፕሎማሲው መሥመርም ላይ ተሰማርተው ለሻዕብያ አመራር የቀኝ እጅና እፍ የነበሩትን የራሱን ኤርትራዊ ወንድሞቹን የቃመ ድርጅት ነው ። ሚኒስትሮች ፣ የወታደራዊ ከፍተኛ አመራር አባላት ፣ ጋዜጠኞችንና የተለየ የክርስትና እምነት ተከታይ ዜጎቹን "የሃገርን ደህንነትና ፀጥታ አሳልፈው ሰጡ" በማለት በድብቅ እስር ቤቶች ውስጥ አሽጎ በማማቀቅ ላይ የሚገኝ መንግሥታዊ ካባን የለበሠ የአፍሪካ ባለረጅሙ ዕድሜ ማፍያ ድርጅት ነው ። ሻዕብያ ፣ ከጭካኔ ባህሪው ሞልቶ የመፍሰስ የተነሳ ከእነዚህ እሥረኞች መካከል ህይወታቸው ያከፈውን እንኳን "እነ እከሌ ሞተዋል" ብሎ ለህዝቡና ለቤተሰቦቻቸው እንኳ የማይናገር በገዛ ህዝቡ ላይ እንቆቅልሽ የሚጫወት የገዳዮች ጥርቅም ነው ። የኢትዮጵያን አንድነት የሚሰብኩ የሚመስሉ መጽሄቶች ስለሚታተሙና መልካም የሚመስሉ የቴሌቬዥንና የራድዮ ፕሮግራሞች ኢትዮጵያዊውን ኢላማ አድርገው ስለሚሰራጩ ፣ የሻዕብያን ለጊዜው የተሸፈነ የሚመስለውን የተፈጠረበትን መሰረታዊ ባህሪን በመዘንጋትና በኢትዮጵያ ህዝብ ጊዜ የማይሰጥ እንገብጋቢ ስቃይ ምክንያት አስቸኳይ መፍትሄ ለማምጣት ወይም ለህዝቡ ለመድረስ በማሰብ ዘሎ ኤርትራ በረሃ ውስጥ መነከሩ በትልቁና በወፍራሙ ሊሰመርበት የሚገባ አጀንዳ ይመስላል ። ከሻዕብያ ስውር አጀንዳ ፎቀቅ እላለሁ ያለ ኢትዮጵያዊ ታጋይ ህይወቱ ተርፏል ከተባለ የመሬት ውስጥ እስር ቤት የዘላለም ቤቱ እንደሚሆን አውቆ በረሃ ቢገባ ጥሩ ነው ።

በእርስ በርስ ጦርነቱ ዘመን ከአንድነት ኃይሎች ጎን ቆመው የኢትዮጵያን አንድነት ለማስጠበቅ ይፋለም ከነበረው ወገን ጋር ሚናቸውን ለይተው የተሰለፉ ኤርትራውያን ነበሩ ። እነዚህ ሰዎች እኮ አንድነትን በመምረጣቸው ሻዕብያ አስመራ ከገባበት እለት ጀምሮ ለረጅም ጊዜያት እስረኞች ነበሩ ። አሁንስ በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ማን ያውቃል? አብዛኛዎቹ ሲቪል ባለስልጣናት እንጂ ወታደራዊ አዛዦችም አልነበሩም ። በተለያዩ ምክንያቶች ከኤርትራ አምልጠው ኢትዮጵያ ውስጥ በሰላም መኖር የጀመሩትን - እድሜ ለወያኔ ወኪሉ - ሻዕብያ በረጅም እጆቹ እንደበግ እየጎተተ ከአራቱም የኢትዮጵያ ማዕዘናት ወስዷቸው የት እንዳደረሳቸው ማንም የሚያውቅ አይመስለኝም ። የክላሽ የውጤት ርቀቱ 4 መቶ ሜትር ነው ይባላል ። ከዚያ ማዶ ፣ ከ4 መቶ ሜትሩ ማዶ ፣ ጠላት ተብሎ ከሚወድቀው ኢትዮጵያዊ ማዶ ማሰብ ጥሩ ነው ። ላውንቸው የመጨረሻ መውደቂያው 5መቶ ሜትር ነው የሚባለው ። የላውንቸሩ ብረተ-እሳት በመጨረሻ ከሚወድቅበት ብረት ለበስ ተሽከርካሪ ባሻገር ስላሉት ኢትዮጵያዊ ሃብቶች ማሰላሰል ደግ ነው ። ከብረት ግብ ግቡ የመጨረሻ ውጤት በኋላ ስላለው ድል ማውጋት ብቻ ሳይሆን የህዝቡን እኩልነትና ተፈጥሮአዊ መብት በእንዴት ያለ አካሄድ ማክበር እና ማስከበር ፤ ሁሉም ዜጋ በእኩል የህግ አዋጆች ያለ አድልዖ የሚዳኝበትን ሥርዓት ማለምም ተገቢ ነው ። በዕድሜያችን ይህን ከላይ ለማለት የሞከርኩትን ዓላማ አድርገው የታገሉና ሥልጣን የጨመደዱ፤ ሳይታገሉም በግርግር በለስ የቀናቸውና ቤተ-መንግሥት አፈፍ አድርገው "አንለቅም!" ብለው የገገሙ ፤ በመጨረሻም በዱላ ብዛት የፈረጠጡ አልያም ደግሞ በስሙኒ ገመድ ህዝቡ ሲጥ ያደረጋቸውን የኛና የብዙ ሃገራትን መንግሥታዊ ሥርዓታትን ሁኔታ አይተናል ። አንዳንዶቹ አሁንም ድረስ ባለስልጣናት ናቸው ። ከነዚህ መንግሥታት ተብዬዎች መካከል አንዱ ደግሞ ያፍሪካው ማፍያ ሻዕብያ ነው ።

ጠንካራ ኢትዮጵያን አፍርሶ ደካማና የሻዕብያ መጫወቻ ዳማ መሆን ጀምራ የነበረችውን ኢትዮጵያን ወያኔ በአደራ ተርክቦ በአደራ ሲያፈራርስና ሲቦዳድስ የነበረው ላፍሪካው ማፍያ ለሻዕብያ ብሎ እኮ ነበር ። ናዝሬት ውስጥ ፣ በአዲስ አበባ - ድሬዳዋ አውራ ጎዳና ላይ እስጢፋኖስ ጋራዥ የሚባል የአንድ ኤርትራዊ ድርጅት ነበር ። ከዚያ ጋራዥ ፊት ለፊት የራሱ የእስጢፋኖስ ንብረት የነበረ ሰፊ ግቢ ነበር ። እዚያ ሠፊ ግቢ ውስጥ የኤርትራንና የተ.መ.ድን ታርጋ ለጥፈው ይታዩ የነበሩ ካሚዮኖች በእያንዳንዷ ምሽት ከኢትዮጵያ ምስራቅና ደቡብ ክፍለ ሃገራት የዘረፉትን ንብረት እንዲሁም ከጅቡቲና ኬንያ በኮንትሮባንድ መልክ የሚያግበሰብሱትን ሃብት ከመኪና ወደ መኪና የሚያገላብጡበት ወቅት ነበር ። የሻዕብያ የስለላ ክፍል የሆነች ቢሮም እዚያው ግቢ ውስጥ ነበረች ። ይህን የመሰለ አፀያፊ ተግባር በስመ-መንግሥት ካባ ሸፋን በግልጽ ሲያከናውኑ ወያኔ ማወቅ ብቻ ሳይሆን ተባባሪም ነበር ። ወያኔ ፣ ኤርትራውያኑ የኤርትራን የነጻነት ቀን በናዝሬት ምክር ቤት አዳራሽ በነጻ እንዲያከብሩ ሲፈቀድላቸው ከበሮና የተለያዩ የሙዚቃ መሣሪያዎችም ጭምር እያቀረበላቸውና አብሮአቸውም እየጨፈረ ነበር ። ይህ ብቻ አልነበረም ፤ "የሌላው

ብሄረሰብ አባላት እንዳይረብሿቸው” በሚል ምክንያት የአዳራሹን ዙሪያ ገባ በከባድ መትረየሶች ወጥረው አላፊ አግዳሚውን “ቀና ብላችሁ እንዳታዩ” ሲሉ የነበሩት የሻዕብያ ጀሌ ወያኔዎች ነበሩ ። ኢትዮጵያን በማፍረሱ ፣ የድሃ ሃብቷን ሌትና ቀን ለሰባት ዓመታት ተግተው ሲዘርፉ የነበሩ እነዚህ ሁለት ክፉና ፀረ-ኢትዮጵያ ቡድኖች መስማማት አቅቷቸው በሁለት አመት ጦርነት 120 ሺ ህዝብ እንኩቶ አድርገዋል። ታዲያ፤ የኢትዮጵያን አንድነት ያነገቡ የወያኔ ተቃዋሚ ኃይሎች ፤ ግፈኛውን የመለስ ዜናዊን አስተዳደር በማስወገድ ዴሞክራሲን ለማስፈን ፣ ፍትህና እኩልነትን ኢትዮጵያ ላይ ለማንሰራፋት ከሻዕብያ ዓላማ በተፃራሪ ተሰልፈው ሳለ ምን አይነት የመንቀሳቀሻ መብትና ነጻነት ነው ከሻዕብያ በኤርትራ ውስጥ የሚቸራቸው? እኔ በበኩሌ ግራ ገብቶኝ ግራ እንዳንጋባ እሰጋለሁ ።

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ለመዋጋት ከአውሮፓ የተሰባሰቡና በአረብ ሃገራት አሳብረው በሻዕብያ ቁጥጥር ሥር በነበረው ነጻ መሬት ወደ አሲምባ ሲያቀኑ የነበሩት የኢህአፓ አባላት አንድ አመት ለሚጠጋ ጊዜ የታገቱት “የኤርትራን መንገንጠል ደግፉ” ተብለው እንደነበር በወቅቱ የሻዕብያ ሰለባ የነበሩት ኢትዮጵያውያን የጻፉትን ካነበብን ቆየን መሰል ። ዛሬ ሻዕብያ መንግሥት ነው ። በረሃ ብቻ ሳይሆን በኤርትራ ምድር ሁሉም ሥፍራ ነው የሚገኘው ። በኢትዮጵያ ጉዳይ የተደራጁ ፣ የሰለጠኑና የታጠቁ የትጥቅ ትግል መራጭ ድርጅቶች በአካለጉዛይ ፣ በሠራዬ ወይም በጋሽና ሴቲት በኩል ወደ ኢትዮጵያ ጠረፍ አካባቢ ሆነው ከኤርትራ መንግሥት ፍላጎት ጋር ባይስማሙ ሻዕብያ እዚያ ለመድረስ የሰዓታት የላንድ ክሩዘር መንገድ ነው የሚሆንበት ። ከራሱ ሉአላዊ ግዛት አልፎ በአፍሪካ ቀንድ ዙሪያ በሚገኙ ሃገራት ውስጥ ከወያኔ መንግሥት ጋር  የአይጥና የድመት ጨዋታ እየተጫወተና እያጫወተ የሚገኘው ሻዕብያ ከነዚህ ኢትዮጵያውያን መሃል የማይመቹት ላይ የጭካኔ እርምጃ ለመውሰድ ወደ ኋላ አይልም ። በጥይት የሚገድለውን ገድሎ ፣ በገመድ የሚሰቅለውን ሰቅሎ ፣ የሚያስረውን አስሮ ደብዛውን ማጥፋት ዛሬ ከሻዕብያ ምንም ማለት አይደለም ። ባህሪው ነው ። ተወልዶበታል ። አድጎበታል ።  ሰርቶበታል - ለአመታት ።

አንድ መሰናበቻ ልጨምር ። አለሚቱ ሻንቆ የምትባል ወጣት ልጅን ክብሮም ካሳ የሚባል አንድ ወጣት ኤርትራዊ ወንጂ ላይ እናቷን በብረት ይቦረቁሰዋል። አለሚቱ ፣ አባትዋ እናቷን ገድሎ የዕድሜ ልክ ተፈርዶበት ወህኒ ቤት ነበር የሚኖረው ። በእውነት አሁን ያለውን የአባቷን ሁኔታ አላውቅም ። በዚህም ምክንያት ገና በወጣትነቷ ሁለት ለመብላት ያላነሱ ራሳቸውን ለመርዳት ያልደረሱ ታናናሽ ወንድሞቿን የመንከባከብ ኃላፊነት የተጣለባት መልከመልካም ነበረች ። በብረት እናቷ ሲተረተር የአውቶቡስ ቲኬት ቆራጭ ሆና በመሥራት ላይ ነበረች ። እሷ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ስትላክ ክብሮም ካሳ ፖሊስ ጣቢያ ተወሰደ ። ግን ፣ ክብሮም ፖሊስ ጣቢያ ብዙም አልቆየም ። በሻዕብያ ረጅም እጆች አማካኝነት በነጻ ተለቆ በአካባቢው ትንሽ ጉራ እንዲነሰንስ ተፈቀደለትና ወደ ሳዋ ለወታደራዊ ሥልጠና አቀና - ለባድሜ ዝግጅት። ምስኪን ኢትዮጵያዊቷ አለሚቱ ግን ከጎኗ ሆኖ አለሁልሽ የሚላት የወረቀት ህግ ሳይሆን የተግባር ህግ አጥታ ፤ ለኢትዮጵያውያን ሽንጡን ገትሮ የሚከራከር ኢትዮጵያዊ የመንግሥት አንድ አካል ጠፍቶ ፣ ጭንቅላ ቷ በስብሶ ፣ ከዚህ ዓለም በግፍ ሞት ተለየች - ሁለቱን ትናናሽ ወንድሞቿን ትታ ።

‘ኤርትራ የተቃዋሚ ኋይሎች መጠለያ መካ መዲና’ ስለተባለች ብቻ እንደገና መሸወድ የሚያስፈልገን አይመስለኝም ። በሻዕብያ መንግሥት እርዳታ ለኢትዮጵያ መልካም ነገር ማምጣት ማለት ከእባብ እንቁላል እርግብ የመጠበቅ ያህል ሆኖ የሚሰማቸው ኢትዮጵያውያን በጣም ብዙ ናቸው ። ይህ ብቻ አይደለም ።  የኢትዮጵያንና የኤርትራን የድንበር ሁኔታ ለመዳኘት ተሰይሞ የነበረው ኮምሽን ባድሜ የኤርትራ ስለመሆኗ ብይን ሰጥቷል ። የሻዕብያ መንግሥት እንደለመደው ታንኮቹን አሰልፎ በፍጥነት እየበረረ መጥቶ ባድሜን መሞጭለፍ አልቻለም ። ሻዕብያ ይህንን ያላደረገው ዲፕሎማት ሆኖ አይደለም ፤ ማፍያ ስለሆነ ነው ። በአስመራ በኩል መምጣት ያለባቸው የሚገድላቸው ኢትዮጵያዊ ድርጅቶችና ኢትዮጵያዊ ዜጎች ያስፈልጉታል ። እነሱኑ እያሰባሰበ ነው ። እነሱኑ እየጠበቀ ነው ፤ ያፍሪካው ባለረጅም ዕድሜው ማፍያ - ሻዕብያ ! !

ፀሐፊውን በዚህ ኢሜይል ያገኙታል : - waqobiya@yahoo.com